جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

تَعْرِيفٌ بِالقُرْآنِ الكَرِيمِ | أمهري | አማርኛ

የተለያዩኢስላማዊ ይዘቶችን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች
አገልግሎት ማኅበር የሊቃውንት ኮሚቴ

تَعْرِيفٌ بِالقُرْآنِ الكَرِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

اللَّجْنَةُ العِلْمِيَّةُ
بِجَمْعِيَّةِ خِدْمَةِ المُحْتَوَى الإِسْلَامِيِّ بِاللُّغَاتِ

የተለያዩ ኢስላማዊ ይዘቶችን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች

አገልግሎት ማኅበር የሊቃውንት ኮሚቴ

بِسْمِ اللهِ الرَّحمَنِ الرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።።

የተከበረው ቁርኣን ምንድን ነው?

የተከበረው ቁርኣን፣ ለሰው ልጆች የተፈጠሩበትን ዓላማ ሊያብራራ፣ በዱንያም ሆነ በመጨረሻውም ዓለም ደስታን ወደ ሚጎናፀፉበት መንገድ ሊመራ፣ ከሞት በኋላ ካለው ዘልዓለማዊ መከራም ነፃ እንዲያደርጉበት የዓለማቱ ጌታ እና ፈጣሪያቸው የነቢያትና መልእክተኞች መደምደሚያ በሆኑት ሙሐመድ ሰለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ላይ ያወረደው የአላህ ቃሉ ነው። ከመጽሃፍቶችም የመጨረሻው፣ ማረጋገጫ እና ያለፉ መጽሃፍቶችን ድንጋጌዎች ሁሉ የሻረ ነው።

ቅዱስ ቁርኣን ዘላለማዊ ምልክትና ተዓምር ነው፤ የአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ነብይ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው። አላህም የሰው ልጆችንና ጂኖችን የቁርኣንን አምሳያ ቢጤውን፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ አንድ ምዕራፍ እንኳ እንዲያመጡ ተወራረዳቸው። ነገር ግን አልቻሉም።

ከ1400 ዓመታት በፊት ከተገለጸበት ጊዜ ጀምሮ የማዛባት እና የመለወጥ እጅ አላረፈበትም፤ እናም በወረደበት የዐረብኛ ቋንቋ ተጠብቆ ይቆያል።የላቀው አላህ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንደሚጠብቀው ዋስትና

ሰጥቷልና።

ቅዱስ ቁርኣን የእስልምና ዋና የማስረጃ ምንጭ ነው፤ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ የሰውን ህይወት የሚያደራጅ እና የሚመራ ህግም ነው። ጥሪውም ብቸኛ የሆነውን ፈጣሪ ወደ ማምለክ ነው። የሰው ልጅ ጌታውን እና ሃይማኖቱን ለማወቅ የሚያስፈልገውን ያብራራል፤ የአጽናፈ ሰማይ ፍጥረት መጀመሪያ እና የሰው ልጅ የፍጥረት ደረጃዎችን ይገልጻል፤ ስላለፉም ይሁን ለወደፊት፣ ስለሚታዩ የሩቅ ሚስጥሮች እንዲሁም ስለቀደሙት ነቢያት ታሪክ የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና አላህ እንዴት እንደረዳቸው እና ጠላቶቻቸውንም እንዳጠፋ ይተርካል። በውስጡ የአምልኮና የግብይት መሠረቶች፣ ወደ መልካም ሥነ-ምግባርም መጣራት፣ ከወራዳ ሥነ-ምግባርም ማስጠንቀቂያን ይዟል። በመጨረሻይቱም ዓለም ስላለው ዕጣ ፈንታ፡- ወይ የምእመናን መኖሪያ ወደ ሆነችው ጀነት ወይ የበዳዮችና

የከሓዲዎች መኖሪያ ወደ ሆነችው ጀሀነም መሆኑን ይገልፃል።

አላህ በዐረብኛ ቋንቋ ባወረደው እና ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲደርስ (እንዲተላለፍ) ካዘዘበት የዚህ ታላቅ መጽሐፍ አስፈላጊነት አንፃር እኛም - ውድ አንባቢ ሆይ! - የቁርኣኑን መልዕክት በቀላሉ እንዲረዱ ለማስቻልና ለማድረስም ሲባል የመልዕክቱን ትርጉም በቋንቋዎ ስናቀርብልዎ እጅግ ደስታ ይሰማናል፤ የስራ ቡድኑ ትርጉሙን ለመረዳት እና

ለመተርጎም የተቻለውን ሁሉ ጥረት አድርጓል። ትርጉሙ የቱንም ያህል ትክክለኛና በጥንቃቄ የተሠራ ቢሆንም ከሰው ሥራ እጅጉን የላቀ የሆነው የቅዱስ ቁርኣን ተአምራዊ ዋና ጽሑፍ (ነስ) የሚያመለክተውን መልዕክት ትርጉም ሙሉ በሙሉ መግለጽ እንደማይቻል በእርግጠኝነት ማወቅ ይገባል። በመሆኑም ቅዱስ ቁርኣን የያዘውን ተጨማሪ እውነታዎች ላይ ለመድረስ ከፈለጉ ቁርኣኑ የወረደበትን ዐረብኛ ቋንቋ እንዲማሩ እንመክሮታለን።

በመልክተኞቹም ላይ ሰላም ይሁን፤ ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው።

የተከበረው ቁርኣን ኢንሳይክሎፔዲያ

www.quranenc.com

የቅዱስ ቁርኣንን ትርጉም በቋንቋዎት ለመመልከት የስልኮን ካሜራ (QR Code) ይጠቀሙ።

* በቅዱስ ቁርኣን ኢንሳይክሎፔዲያ ድህረ ገጽ (www.quranenc.com) ላይ በእያንዳንዱ አንቀጽ ፊት ለፊት ባለው የማስታወሻ መስከት ትርጉሙን መሻሻል ያሎትን ጥቆማዎችና አስተያየት ስንቀበል በደስታ ነው። እኛን ማግኘት ከፈለጉ በኢሜል ሊልኩልን ይችላሉ፡-

info@quranenc.com

***


جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

